

# ጳውሎስ ከኤፌሶን ሄደ

- ከደቀመዛሙርቱ ጋር በጢሮአዳ ከተማ በሰንበት ዕለት ተገናኙ። በዚያም በአንድ ሕንፃ በላይኛው ክፍል ውስጥ ይሰብክ ነበር። እስከ እኩለ ሌሊትም ያለማቋረጥ ተናገረ። ስሙ አውጤኪስ የተባለ አንድ ወጣት መስኮት ላይ ተቀምጦ ነበር። ከስብከቱ ርዝመት የተነሳም እንቅልፍ እንቅልፍ አለውና ተኛ። መስኮቱ ተከፍቶ ስለነበርም ወደታች ወደመሬት ወደቀ።
  ወደታች ሄደው ሲያነሱትም ሞቶ ነበር።

- ጳውሎስም ወደ ምድር ፎቅ ወረደ።
  አውጤኪስ እንደገና ሕያው በመሆኑ ሰዎች ሁሉ ተደሰቱ።

- ጳውሎስ ሚጢሊን ወደሚባል ቦታ እንደደረስም በኤፌሶን የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወደእርሱ እንዲመጡና እንዲገናኙት መልእክት ላከባቸው። በአንድነት ተሰብስበው ሳሉም አንዳንድ ነገሮችን ነገራቸው። በመጀመሪያ እንዴት እውነትን እንደሰበከላቸው አስታወሳቸው። በኢየሩሳሌም ስደትና መከራ እንደሚጠብቀው ያውቃል። ስለዚህም መንጋውን በመጠበቅ ረገድ ጥሩ እረኞች እንዲሆኑ አሳሰባቸው።

- “ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው፣” የሚለውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርትም አስታወሳቸው።

- ጳውሎስም ከእነርሱ ጋር ተንበርክኮ ፀለየ። ሁሉም አቅፈው እየሳሙት አለቀሱ።
  እንደገና እንደማይገናኙ ሲያስቡም እጅግ በጣም አዘኑ። ከዚያም ወደመርከቡ ሄዱ። ጳውሎስም ተለይቷቸው ተጓዘ።

*ይህን ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20፡1 – 38 ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።*

Copyright picture courtesy of gospelservices.com
http://gardenofpraise.com